# ክርስቶስ በስምህ

ክርስቶስ በስምህ ይዘናል ቀኖና፣
ስቅለት ትንሣኤህን እናያለንና፡፡
ጾም ማለት እንግዲህ ይህ ነው ስርአቱ፣
ሐዋርያት ጾመው ለኛ አበረከቱ፡፡
ነፍስና ሥጋችን በምግብ ተጣልተው፣
ሽማግሌ ሆኖ ጾም አስታረቃቸው፡፡
አብረው እያደሩ አብረው እየዋሉ፣
አያምርም አይመስልም በመብል ሲጣሉ፡፡
ነፍስም ከሥጋዋ መለየቷን አውቃ፣
የአለም ተድላዋን ደስታዋን ንቃ፣
በጾም በሱባዔ ትኖራለች ታጥቃ፡፡
ነፍስም ለሥጋዋ ትመክረው ጀመረች፣
በብዙ ምሣሌ እያመሳሰለች፡፡
ሥጋዬ ሞኝ ነህ መብልን አትውደደው፣
ከአዳም ጀምሮ ከመጀመሪያው ሰው፣
መብል ሲጎዳ እንጂ ሲጠቅም መች አየኸው፡፡ (፪)

www.HolyTrinityEOTCNY.org